

## READY TO WORK (RTW)

በኢኮኖሚያዊ መረጋጋት ጎዳና ላይ ላሉት አዲስ ሰፋሪዎች እና ስደተኞች እንግሊዘኛ መማር እና ጥሩ ስራ ማግኘት ሁለቱም ወሳኝ እርምጃዎች ናቸው። ለዚህም ነው Office of Immigrant and Refugee Affairs (OIRA) Ready to Work (RTW) ን ያዘጋጀው። RTW እንግሊዘኛን ለሌሎች ቋንቋዎች ተናጋሪዎች (ESOL) ክፍሎች፣ የኮምፒውተር እና ዲጂታል እውቀት፣ የስራ ዝግጁነት፣ እና በ ብዙ ቋንቋ የሚቀርብ፣ ባህልን እውቅና የሚሰጥ እና ብቁ የሆነ የጉዳይ አስተዳደር አገልግሎቶችን በማጣመር አዲስ ሰፋሪዎች እና ስደተኞችን በተሳካ ሁኔታ ለማገልገል የሚሰራ ማህበረሰብን መሰረት ያደረገ ፕሮግራም ነው።

Seattle Office of Immigrant and Refugee Affairs

### ስለ እኛ

የ Office of Immigrant and Refugee Affairs (OIRA) ተልዕኮ የሲያትል አዲስ ሰፋሪ እና ስደተኛ ማህበረሰቦችን በፖሊሲዎች፣ በፕሮግራሞች፣ በአገልግሎቶች እና የማህበረሰብ ተሳትፎ በኩል ሕይወታቸውን ማሻሻል ነው።

**የእውቂያ መረጃ:**

(206) 727-8515
seattle.gov/iandraffairs/RTW

seattle.gov/iandraffairs
twitter.com/iandraffairs
facebook.com/iandraffairs

### ስለ Ready to Work (RTW)

RTW በ 2015 ውስጥ፣ በተለይ እንግሊዘኛ ለመማር እና ሥራ ለማግኘት ከፍተኛ እንቅፋት ለሆነባቸው ነዋሪዎች እንደ አንድ የእንግሊዝኛ ቋንቋ መማሪያ እና የስራ ስልጠና ፈጠራ ሞዴል ሆኖ የተዘጋጀ ነው። ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ፣ ብዙዎቹ ተሳታፊዎች ጥሩ ሥራ በማግኘት እና በአካባቢያዊ የማህበረሰብ ኮሌጆች ወደ ከፍተኛ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ደረጃ ትምህርታቸውን ቀጥለው፣ ከ1,000 በላይ አዲስ ሰፋሪዎች እና ስደተኛ ሥራ ፈላጊዎች በፕሮግራሙ ተሳትፈዋል።

### RTW ሀገር አቀፍ እውቅና አግኝቷል

በ 2016 ውስጥ U.S. Department of Labor እና National Skills Coalition ሁለቱም የሰው ሀይል እና የጎልማሶች ትምህርት የገንዘብ ድጋፍን የስደተኞችን የስራ ሀይልን የመጠቀም ሚዛን በመደገፍ Ready to Work ን እንደ ሀገራዊ ምርጥ የተግባር ተምሳሌትነት አድርገው አጉልተው አሳይተዋል።

### የRTW አጋር ድርጅቶች

- Asian Counseling and Referral Service (ACRS)
- HomeSight
- Literacy Source
- Neighborhood House
- Somali Community Services of Seattle

### RTW እንዴት እንደሚሰራ

RTW አዲስ ሰፋሪዎች ጥሩ ስራዎችን እንዲያገኙ እና በኢኮኖሚያዊ በራስ መቆም እንዲችሉ ለማስቻል የESOL ክፍሎችን ከኮምፒዩተር እውቀት ትምህርትን ከ የጉዳይ አስተዳደር ጋር ያጣምራል። ሥርዓተ ትምህርቱ ከኮሌጅ እና ከ ሞያ ዝግጁነት ደረጃዎች ጋር የተጣጣመ ነው። እነዚህ የሲያትል ድርጅቶች ዓመቱን ሙሉ ትምህርቶቹን እና የጉዳይ አስተዳደር አገልግሎትን ይሰጣሉ:

#### ሰሜን ሲያትል (North Seattle)

**Literacy Source**
literacysource.org
(206) 782-2050

#### ደቡብ ምስራቅ ሲያትል (Southeast Seattle)

**Asian Counseling and Referral Service (ACRS)**
acrs.org
(206) 805-8950

#### ምዕራብ ሲያትል (West Seattle)

**Neighborhood House**
nhwa.org
(206) 294-2009

የ Ready to Work ትምህርቶች በየሩብ ዓመቱ የሚሰጡ ናቸው። ምዝገባን በተመለከተ ተጨማሪ መረጃን ለማግኘት ከዚህ በላይ ካሉት ማንኛቸውም ቁጥሮች ላይ ይደውሉ።